# የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል

በዚህ ጉዳይ ላይ ለመጻፍ ያነሳሳኝ አባ ሰላማ (www.abaselama.org) በተባለው ድረ ገጽ ላይ "ግብጻውያን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተሐድሶ እንደሚያስፈልጋት የጠቆሙበት ሥልጠና" በሚል ርእስ የሰፈረውን የማወናበጃ ቅስቀሳ በመቃወም ነው።

ባለፈው ዓመት ታኅሣስ ወር 40 አባላት ያሉት የግብፅ ኮፕት ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ለ5 ቀናት የዘለቀ ሥልጠና ለመስጠት መምጣታቸው ተገልጿል። የግብፃውያኑ የአሠልጣኝነት ተልእኮ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ራሷን የምታስተካክልበቸውና ተሃድሶ የምታደርግባቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉባት" ጥቆማ የተደረገበት አጋጣሚ ነበር ተብሏል።

ከሁሉ በተቀዳሚ ያውሮፓ ክርስቲያን ተብዬ ወገኖችና አገር በቀል ምልምሎቻቸው ኢትዮጵያዊነት የሚንፀባረቅባቸውን ምልክቶችና ተቋሞች ሁሉ ማስጠፋትና ማዳካም እንደ ዋና ስልት ይዘውታል። የመንግሥታችን አርማ አንበሳው፣ ጥንታዊው የግእዝ አማርኛ ፊደል፣ ወዘተረፈ ተዘምቶባቸዋል።

ኢትዮጵያዊነት የማጥፋት ዘመቻ ውስብስብና ዘርፈ ብዙ ነው። ታሪካዊ መነሾም አለው። አውሮፓዊና አረባዊም እጅ ያለበት ሲሆን ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዎ ተልዕኮዎች አሉት።

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ የዳበረ ባሕል፣ የሚታይና የሚዳሰስ የረጅም ዘመናት የታሪክ ቅርስ፤ በኢትዮጵያዊነቱ የሚተማመን ኩሩ ሕዝብ ያላት አገር ናት። የኢትዮጵያ ሕልውና ለአፍሪቃውያን የነፃነት ትግል ከፍተኛ የመንፈስ ጥንካሬ በመስጠቱ ሳቢያ ለጥቁር ሕዝብ ዘርያና ለአፍሪቃዊነት ንቀትና ጥላቻ ላላቸው ዘረኛ ኃይሎች ሁሉ የውስጥ እግር እሳት ነው።

የአውሮፓ ቅኝገዥዎችና ተስፋፊዎች የጥቁር ሕዝብን እኩልነትና ነፃነት ስለማይቀበሉ የኢትዮጵያን አርአያነት ለማዳከም ሲሉ የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት የረጅም ዘመናት ታሪክና ሥልጣኔ ከዘመነ ፈርኦን ሥርዎ መንግሥት ምስረታ ጀምሮ የነበረውን እንዳልነበረ በመቁጠር፣ ይልቁንም አፍሪቃዊ ሥር መሠረቱን በመካድና ፍጹም የፈጠራ ወሬ ማለትም የአረብ ሴማዊ ተብዬ ሰፋሪዎችን አሰልጣኝነትና የአክሱምን ጥንታዊ ሥልጣኔ ፈጣሪነት ተረት ተረት ሲያናፍሱ ቆይተዋል። ጥቁር ሕዝብ በአፍሪቃ የረቀቀና የመጠቀ ባሕልና ሥልጣኔ መሥራት እንደማይችል በሰፊው ተለፍፏል።

አፍሪቃዊ ተቋማትን፣ ባሕልና ልምዶችን ሁሉ በማናናቅ አሶግዶ በአውሮፓዊ ተቋም ለመተካትና በቅኝገዥነት ለመቆጣጠር ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ ሲደረግ የቆየውና የሚደረገው ዘመቻም መታየት ያለበት ከዚሁ አንጻር ነው። ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ያውሮፓ ኮተሊክ ክርሲትያን ነንባዩች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶን ለውጠው የነሱ የበታችና የነሱ አይነት ክርስትናን ከአልተቀበልን በስተቀር ከግብፅ እስላማዊ ተሰፋፊው እስማኤል ፓሻን ወራሪ ጦር ጋራ በመወገን የስለላ መረጃ አቅራቢው የነበረው፣ ባጤ ቴዎድሮስና ባጤ ዩሐንስ ዘመነ መንግሥት የካቶሊክ ሚሲዩን ቅጥረኛ ሙሲንጅር ዋርነር በጀግናው የአፋር ሕዝብ ታጁራ አጠገብ የተገደለውና ሌላው የፕሮቴስታንት ሚሲዩን የሐን ክራፍ የተባለው ከሰሜን ኢትዮጵያ ሲባረር በታጁራ በኩል ሸዋ ገብቶ ከሸዋ በስተደቡብ ያሉትን የወረሞን ልዩ ልዩ ጎሣዎች የፕሮቴስታንት ክርስትና ለማንሳት እንዲሁም ከአበሻ በስተደቡብ በጋሎች መካከል ያለው ውብ ሥፍራ ለብዙ ሽህ አውሮፓውያን ሠፋሪዎች እንደ አሜሪካ፤ አውስትራሊያ፣ ኒውዘላንድ፣ ካናዳ ሰፊ እድል ይከፍታል በማለት ክራፍ ተመኝቷል። ሸዋም ዳግመኛ እንዳይገባ ስለተከለከለ ጉዞውን ወደ ዛንዚባር አድርጎ ምሥራቅ አፍሪቃን ለእንግሊዝና ጀርመን ቅኝገዥዎች በወንጌል ሽፋን አሳሽ መንገድ ጠቋሚ የነበረውን ያስታውሷል። የእንግሊዝ ጦር ወደ መቅደላ ሲዘምት የሐን ክራፍ መረጃ ሰብሳቢ ሰላይና አማካሪ በመሆን ተሳትፏል። ባቀናበረው ሐተታ ጋሎች "ኦርማኒያ" ተብለው እንዲጠሩም ሃሳብ አቅርቧል። ( ... the Gallas have no general name to indicate their nationality or its seat, I propose to include under the desigination of "**Ormania**" J Lewis Krapf: Travels Researches and Missionary Labour During an eighteen years Residence ( London , 1968) 2nd ed , p. 73)

የተናቀች አገር በአህያ ትወረራልች እንዲሉ የግብጥ ኮፕት ተብዬ ያረብ፣ የግሪክና የሮማውያን ክልስ ክልስልስ መጢቃ ውላጆች ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ነገረ መለኮት ሊያስተምሩን ተቀናጡ። ምጥ ለናቷ አስተማረች ይሏል ይህ ነው። ኮፕቶች ሁለት ጾም ማለትም ሁዳዴና ፍልሰታ ብቻ ስላላቸው ዓርብና ረቡዕ ስለማይጾሙ ጾመ ነቢያትን ሆነ የኛን ሰባት አጽዋማት ሕግና ሥርዓት የማያውቁ ሁሉን አግበስባሽ አሳማዎች ስለ ጾም "ሥልጠና" ለመስጠት መከጀላቸው ከቶ አያስገርምም። የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል ነውና ፀረ ኦርቶዶክ ተዋህዶ ወገኖች ሁሉ የተፈጠርውን አጋጣሚ ለመጠቀም አሰፍስፈዋል።

በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው በወያኔ ሻእቢያ መንግሥት ተብዬው ፀረ ኢትዮጵያ ቅጥረኛ ድርጅት የሚደገፉት ሕጋዊ እውቅና አግኝተው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ

ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ የጥቃት ኢላማቸውን አነጣጥረዋል። በእምነት ነፃነትና እኩልነት ሽፋን አዲስ መጤ ልዩ ልዩ የክርስቲያን ድርጅት ነንባዩች በተግባራቸው ግን ፍጹም ክርስቲያን ያልሆኑ ግብረ ሰዶማውያን፤ ሃይማኖትን አገር ለመንጠቂያ፤ ሕዝብን ለመከፋፈያ ዋና መሣሪያ አድርገው ሲቅነዘነዙ እነሆ በዓላም ላይ ብቸኛ ጥንታዊ የጥቁር ሕዝብ ቤተ ክርስቲያናችንን "ያረጀች ያፈጀች፣ የዘመኑን ሥልጣኔ ተብሎ የሚደረገውን ፀረ ተፈጥሮ ገደብየለሽ መበላሸት ለመቀበል ራሷን ያላዘጋች አሮጌ ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች እድሳት ያስፈልጋታል" በማለት የኑፋቄ ትምህርታችውን ይዘው ወደ ቤተክርስቲያን በመግባት <u>ተሃድሶ ኦርቶዶክስ</u> የተባለውን ማኅበር መሥርተው በወያኔ የሽግግር መንግሥት ሕጋዊ እውቅና በታህሳስ ወር 1983 ዓ.ም ማግኘታቸው ይታወሳል። ማኅበሩን ያቋቋመው አባ ኃይለ ልዑል ቦጋላ የተባለው ቅጥረኛ በገዳማ ሲኖር በራእይ ኦርቶዶክስን ወደ ፕሮቴስታንት ክርስትና ተብዬ እንድቀይር ታዝዤ ነው እያለ ሲያወናብድ ነበር። የጀርመን ኮተሊክ መነኩሴ የነበረው ማርቲን ሉተር እንዴት ያልተከላለሰው ንጹሕ አረመኔው የጀርመን ዘርያ አሕዛብ በቅይጥይጥ ሮማውያን ውላጆች ሥር ይገዛል የሚል የሥልጣንና የጥቅም ሽኩቻ ሳቢያ ፀረ ካቶሊክ እንቅስቃስ በመሳፍንቶችና ንጉሦች ተባባሪነት ይፋ ተቋውሞ ተስፋፍቶ ሉተርም የኮተሊክ ምንኩስና ቆቡን ጥሎ ሚስት አግብቶ ብዙ ልጆች ወልዷል። የሉተር ተሃድሶ ቅስቀሳ በአደባባይ ሲሆን ዛሬ በኢትዩጵያ የሚደረገው ግን በሚስጥር ነው። መታወቅ ያለበት ሐቅ ፕሮቴስታንቶች ከካቶሊኮች ጋራ በዶክትሪን ማለትም በቅኖናዎች አንድ ናቸው። የሚለያዩት በሕገ ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓት ነው። የኮተሊክ ዋና ከተማ ቫቲካን ሲሆን አገሯ ግን መላው አውሮፓ ነው። በሮም ከተማ የቅዱስ ጴጥሮስ ካቴድራል ሲታነፅ የገንዘብ መሰብሰቢያ የተጻፈውን ደብዳቤ ልፈፋ ጽድቅ ባንገቱ ላይ አሸንክታብ የሚያደርግ በቀጥታ መንግሥተ ሰማያት ያስገባል ተብሎ ይሸጥ የነበረውን ምክንያት አድርጎ ማርቲን ሉትር የመለያየቱን ጦስ ነዛው። በዚያውኑ ወቅት ተቃውሞው በፈረንሳይና ሲዊዘርላንድ ተስፋፋ። ቀጥሎም የእንግሊዙ ንጉሥ ሄነሪ ስምተኛ ተብይው የሕግ ሚስቱን ትቶ ሌላ የምወዳትን ቁባት ከአለገባሁ የሮማ ካቶሊክነትን አልፍልግም በማለት ተለይቶ የራሱን ቤተ ክርስቲያን የአንገሊካን ብሎ ሰይሟል። ከዲያቆን እስከ ሊቀ ጳጳስ ባለሚስቶች የሆኑባት ናት።

ንግባእኬ ኀበ ጥንተ ነገር በሥልጠናው ላይ የተነሳው ሌላው ጥያቄ ግብፃውያን ታቦት የላቸውም። ለምን ኢትዩጵያ ብቻ ታቦት ይኖራታል? ስለዚህ ተሃድሶ በማድረግ ታቦትን እንተው የሚል አንደምታ ተዘግቧል።

ጽላት ማለት አሠርቱ ቃላትና የእግዚአብሔር ኅቡዕ ስም የተጻፈበት ሰሌዳ ነው። የሰሌዳው ማደሪያ ወይም መያዣ ሳጥን ታቦት ይባላል። ጽላተ ሙሴ ወይም ታቦተ ጽዮንም ይባላል።

ታቦተ ጽዮን በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ኢትዮጵያ መጥታለች። ከስድስት መቶ ዓመታት በላይም ጣና ሐይቅ ውስጥ ከሚገኘው ደሴት ጣና ቂርቆስ ውስጥ ኖራለች።

የጽላት አክብሮት የመጣውና የተጀመረው በብሉይ ኪዳን ሕግ ነው። ኢትዮጵያም ይህን ባሕል አክብራና ጠብቃ ይዛለች። ጽላትን በማክበርና በመጠበቅ ብቸኛዋ አገር ኢትዮጵያ ናት። በዚህም እንኮራለን። የኛን ጽላት ጣኦት ነው የሚል ፈረንጅ ይሁን ቅጥረኛ ድንቆሮ ገደል ይግቡ። ሐሰተኛና ምቀኛ አፉችሁን አድሱ። "በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ተሃድሶ" እያላችሁ የምትወሻክቱ መናፍስተ ርኩሳን የአሳማ ፈረንጅ ቅልብ በቀቀን ሁሉ አደብ ግዙ። የኢት□ጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የራሷ መጽሐፍ ቅዱስ አላት። መጽሐፍ ቅዱስን በቅድሚያ በራሷ ፊደልና ቋንቋ ከእእዘጋጁት አገሮች አንዷ ናት። የኛ መጽሐፍ ቅዱስ ከሁሉም ልዩ የሚያደርገውና ከማንኛውም መጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ ብዛት ያለው 81 መጻሕፍትን መያዙ ብቻም ሳይሆን እንደ መጽሕፈ ሄኖክ ያሉት የሚገኙት በኛ ብቻ ነው። ሰው ከሆናችሁ አንገታችሁን ድፉና ንስሐ ግቡ። ወገኛ ይንገሩኝ ባይ ሁሉ የምትቀባጥሩትን አታውቁትምና ይቅር ይብላችሁ። በመጀመሪያ እራሳችሁን ከፈረንጅ የአምሮ ባርነት ነፃ አውጡ። በራሳችሁ ሕሊና ማሰብና ማገናዘብን ተማሩ።

እረ! ለመሆኑ ማነው መጽሐፍ ቅዱስን የከለሰውና የበረዘው? በተለይ ደግሞ ፕሮቴስታንት ተብዬ የጎግ ማጎግ ዘርያዎች እንኳን ጽላትና ሕገ ቤተክርስቲያንም ይቅርና መጽሐፍ ቅዱስን ገነጣጥለው፣ ከልሰው በርዘው አይደለም እንዴ እንደ አበደ ውሻ የሚቅነዘነዙት የባሕል ተፅዕኖና የኢኮኖሚ ጥቅም ለማግኘት ነው!

መጽሐፍ ቅዱስ በአውሮፓ አረመኔያዊ አሕዛብ ዘንድ ሲደርስ የፖለቲካ ካራ ወይም ሳንጃ ሆኖ ሠርቷል። የጥቁር ሕዝብ በአፍሪቃ፣ በአውስትራሊያና ታስማኒያ፣ በደቡብና ሰሜን አሜሪካ ነባር ሕዝቦች ታርደውበታል፤ ነፃነተቸውን ተገፈዋል። እኛ ዓይናችንን ጨፍነን እንድንጸልይ ሲነግሩን ለም መሬታችንን ወስደውታል በማለት የኬኒያ የነፃነት አባት ጆሞ ኬኒያታ የተናገሩትን ማገናዘብ ይጠቅማል።

ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው በትንቢት ስትጠብቀው የቆየችውን መሲህ ነበር እንጂ እንደ አውሮፓውያን አረመኔ አሕዛብ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሃ ፈሳሽ ድንገት የተሰበከላት አይደለም።

ሰብአ ሰገል የጥበብ ሰዎች ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ወርቅ ዕጣንና ከርቤ በመያዝ ሄደው ሰግደውለታል።
ኢትዮጵያዊያን በሃምሳኛው ቀን በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት አምነው ከተቀበሉት መካከል ነበሩ። ሕዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ኃየል ተመልተው የኢትዮጵያን ቋንቋ ሲናገሩ ሰምተውና ተገርመው የክርስቶስን መሞትና ትንሣኤ አረጋግጠው ተመልሰዋል። ኢትዮጵያዊ ጀንደረባ በእግዚእብሔር መልአክ ትዕዛዝ በፊሊጶስ እጅ መጠመቁ፣ ሃይማኖት በኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተመሠረተኛ የጸና ነው።

የግብፅ ኮፕት ቤተ ክርስቲያን የኢትይጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን አልመሠረተችም። ያለን ግንኙነትም በአሌክሰአንደሪያው ሕዋሪያ መንበረ ማርቆስ ብቻ ነው። ከግብፅ ሲመጣ የነበረው አቡንም በኛ ነገረ መለኮትና አስተዳደር ምንም ሥልጣን አልነበረውም። የቤተ ክርስቲያኛ ቅኖና ትምህርት ዓቃቢያን የሆኑት ያገሩ ተወላጅ እጨጌዎች ነበሩ።

ኢትዮጵያ ከማንም ምንም የሃይማኖት ልምድ አትፈልግም።

መናፍስተ ርኩሳን ወግዱ! ከማኅበረ ምዕመናን ራቁ!

ስብሓት ለእግዚአብሔር ‼

ኢትዮጵያ ታብጽሕ እደዊሃ ሃበ እግዚአብሔር።

አባ ክፋይ ተለአለ ደባልቄ